# ሚስቶችን የሚነካካ ሰይጣን

# በአትላንታ ሰበካ አለ ይባላል

# አውነቱ ይውጣ!

ከግደይ ገ/አግዚኣብሔር

አንድ መነኩሴ ይችን አለም ካልተው፡-ከሥጋዊ ፈቃድ ካልተላቀቀ፡ መንፈሳዊና ቅድስና ሕይወቱን በጽህና ካልጠበቀ፡ አግዚአሔርን ያሳዝነና የምእመናንን  እምነት ያጎደፈ ሥራ ይሰራል ማለት ነው።

እንድህ አይነት መነኩሴ ንሥሃን ዋናኛ መድህን አድርጎ ከአግዚኣብሔርና ከምእመናን ጋር በመታረቅ ፈንታ በትእቢተኛነት ኃጢኣትን እያበዛ መኖርና ሲጋለጥ ደግሞ በሰይጣን ማሳበብ ልቡና ፍቅር-አግዚኣሔር የሌለው የማይጸጸት ከይሲ ሰው ነው ማለት ነው። በቀል የእግዚአብሔር ነው፡  እንድህ እይነቱ መነኩሴ ከአምላክ ዘለአለማዊ ቅጣት አያመልጥም። የእግዚአብሔርንም መንግስት አይወርስም።

የመነኩሴ ሰይጣናዊ ተግባርና አለማዊ ኃጢአት ሲነሳ የሩስያው  ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መነኩሴ አባ ግሪጎሪ ራስ ፑቲን ትዝ ይለናል።

መነኩሴ አባ ራስፑቲን በዝሙት ቁራኛ ተለክፎ መንፈሳዊ ሕይወቱንና ቅድስናውን በንጽህና ያልጠበቀ፡ በየዋህነት የእግዚአብሔር ሰው መነኩሴ ነው ብለው የቀረቡትን የነደፈ፡ ሚስቶችን ያወሰለተ፡ እቴጌ አሌክሳንድራ ሳይቀሩ የሩስያን ንጉሳዊ ቤተሰብ፡ ወይዛዝርትንና የመካንት ሚስቶችን በፍትወተ-ስጋና በዲሪያ ያረከሰ ከይሲ መነኩሴ ነበር።

በዚህ ተግባሩ በሩስያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፡ እምነትና ታሪክ ላይ አሳፋሪ ጥቁር ነጥብ በመጣሉ መጀመሩያ ላይ ከኮሚኒስቶች መርዝ ቢያመልጥም ኃላ ግን በሃይማኖት ተቀርቁርና በወግ አጥባቂ መሳፍንቶች ሴራ ተገድሎ ሴንት ፒትስበርግ ቦይ ውስጥ ተጥሏል።

ተግባረ- ራስ ፑቲን አይነት ድርጊት የተወገዘ ቢሆንም እዚያ ማዶ አትላንታ በሚሏት አገር አሁን ተሰምቶ ሰው ሁሉ ጉድ ብሎኣል። መቼም በሃይማኖትና በእምነት ቀልድ ስለሌለ አውነቱ ይውጣ። ነገር ግን የሚመለከታቸው ወገኖች ሁሉ አውነቱን ማውጣት ተፈራርተው በሬድወ ላይ እንቀርብም

በማለታቸው ሚስቴን ቤተ ክርስቲያን መላክ ወይንም ይዤ መሄድ ፈራሁ እያሉ ምእመናኑ ሥጋቱን በቀልድ እየገለጸ ነው።

አንዳንድ ሰባኪዎች ጉዱ ቢገርማቸውም የቅዱሳን አባቶችን ጉዳይ ተሸፋፍኖ እንድያዝ ይሰብካሉ። ምናልባት ይህ ስብከት ምን-ካምን ያለበት ዝሊያ አይችልም እንደሚባለው ሊሆን ይችላል። ያንዳንድ መነኩሳት ፈተናን አለመታገስ ከራሳቸው ድክመት ብቻ ሳይሆን ቀርበው ከሚያለቀልቁና በቀላሉ ከሚነተቱ የዋህ ምእመናን ጭምር ይመስላል። ለማንኛውም ሰይጣንን ለማሸነፍ የእምነታችንን ንጽህና ለመጠበቅ እውነቱ ይውጣ።

01/27/2012